# <u>ወንጀል እንደሊሻን</u>

## ከመስፍን ወልደማርያም

## ቃሊቲ

በመጀመሪያ ዱሮ በአንድ ፍርድ ቤት ውስጥ ለማዳመጥ ገብቼ የሰማሁትን ልናገር አንድ ሰው ሌላውን በአንድ ሺህ ብር ከሶታል። ተከሳሹም ደሞ ሳንቲም የለብኝም ይላል:: ከሳሹ ከጠበቃው ጋር በመሆን ላቀረበው ክስ ማስረጃ አድርጎ ያቀረበው ከሳሹ ራሱ ለአንድ ጓደኛው የፃፈውን ደብዳቤ ነው:: ተከሳሹ በመደነቅ ይህ የእኔ ከሳሽ ደግ ሰው በመሆኑ 1000 ብር ወስኖ እንጂ አንድ ሚልዮን ብር አለብህ ቢለኝ ማን ይከለክለዋል በማለት በፌዝ ተናገረ:: እኔ ዳኛው ፋይሉን ዘግተው ለተከሳሹ ኪሣራ ቆርጠው ያሰናብቱታል ብዬ ስጠብቅ ዳኛው ሌላ ማስረጃ አቅርብ ብለው በቀጠሮ አሳደሩት::

በዚህ ክስ ላይ የህግ ሥርዓቱን ያበላሹት በመጀመሪያ ከሳሹና ጠበቃው ናቸው:: ከዚያ በኋላ ፍርድ ቤቱ ከማረም ይልቅ ነገሩን በማጓተት የፍርድ ሥርዓቱን በተጨማሪ ግድፈት አበላሸው:: ይህንን ይዘን አሁን በቅንጅት መሪዎችና አባሎች በጋዜጠኞችና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች መሪዎች ላይ የቀረቡትን ክሶችና የፍርዱን ሂደት እንመልከት::

ክሶቹ ሰው ሁሉ ስለሚያውቃቸው አልዘረዝራቸውም:: ነገር ግን ክሶቹ ከላይ በፍትህብሔሩ ችሎት እንደገለፅሁት የከሳሽ ዓላማ በትንሹ የተጠና ሳይሆን ተከሳሾቹን ለመደፍጠጥና ለመጨፍለቅ የተተለመ ነው። ይረሳል እንጂ፣ መደፍጠጥና መጨፍለቁ እርቃኑን በወጣ ጭካኔ በተለይ በወጣቶች ላይ ተፈፅሟል:: የታሠሩት የተሻለ ዕድል የገጠማቸው ናቸው:: የተገደሉት በሕገ አራዊትነት ተጨፍጭፈዋል:: ከሳሽ ገና ከመጀመሪያው የክሱን ዓይነትና የቅጣቱንም ክብደት በአደባባይ አሳውቋል:: ዐቃቤ ሕግ የሚባሉት የከሳሽ ጠበቆችም የከሳሹን ትእዛዝ ተቀብለው የክስ ክምር አቅርበዋል:: የክሱን ክምር በሕጋዊ ሥርዓት ለማጣራት ችሎታ ያነሳቸውን ያህል ተከሳሾቹንም ለማበጠር ስለተሳናቸው በያለበት ያገኙትን ስም ሁሉ ከአውሮፓና ከአሜሪካ ጭምር በመከመር የተከሳሾቹን ዝርዝር አሳብጠውታል:: ለከሳሾች ጠበቆች ትልቁ ነገር ክሱንና ተከሳሾቹን መከመር ብቻ ነው:: አሜሪካ ተቆጣና የተከሳሾቹ ክምር ተናደ:: እንዲሁም አንዱ ክስ ትንሽ ተቀረፈለት:: የከሳሽ ጠበቆች በፍርድ ቤቱ ውስጥ ያሳዩት ሥነ ምግባር ለእኔ የሚያሳፍረኝ ነበር:: ፍርድ ቤቱ ከተሰየመ በኋላ በግርማ ሞገስ ይገባሉ:: በተከሳሾች ላይ አስቀድመው ወስነው "አድመኞች" አንዳንዴም "ወንጀለኞች" እያሉ ሲናገሩ ቆይተዋል:: የሦስቱ ተከሳሾች ጠበቆች ተቃውሞ አቅርበው ፍርድ ቤቱ ግዜ ወስዶ የከሳሽ ጠበቆችን አረማቸው:: እነሱን የሚያካክሉ ልጆች ያሏቸውን ሽማግሌዎች ተራ ጨዋነት በጎደለው አነጋገር ሲዘረጥጧቸው ኩራት ይሰማቸው ነበር:: የተዋረዱት እነሱ መሆናቸውን ሳያውቁት አዋረድናቸው ብለው ያብጡ ነበር:: ራሳቸው ለምሥክርነት ያቀረቡት ሰው ስላጋለጣቸው የአእምሮ ሕመምተኛ ነው በማለት ስሙን አጠፉት:: የከሳሽ ጠበቆች እንዲህ ያሉ ናቸው::

ከክሶቹ ሁሉ የሚያቅለሸልሸውና የሚከረፋው የትግሬን ዘር ማጥፋት የሚለው ነው:: ሌሎች ክሶች ሁሉ ከፍርድ ጋር ያልፋሉ የትግሬን ዘር ማጥፋት የሚለው ግን

# ወንጀል እንደሊሻን

ከመስፍን ወልደማርያም

## ቃሊቲ

መርዙ ሊቆይ የሚችል ነው:: ተከሳሾቹን ለዓመታት አሥሮ ለማቆየትም ሆነ ለመግደል ይህ ክስ በፍፁም አስፈላጊ አይደለም::

የተፈለገው የትግራይ ተወላጆችን በማስፈራራትና ሥጋት ውስጥ በመጣል ወደ ወያኔ እንዲጠጉ ለማድረግ ነው:: ይህ እኩይ ክስ ተከሳሾቹን ጭራቅ በማስመሰል የፖለቲካ ጥቅም ለማግኘት የታቀደ ነው::

የከሳሾች ጠበቃ ለክሶች ያቀረባቸው የአድማ ማስረጃዎች በምርጫ ውድድሩ ግዜ በቪድዮ የተነሱ ስብሰባዎች፣ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የተላለፉ ክርክሮች፣ በጋዜጣ የወጡ ፅሑፎች ናቸው:: እንኳን የሕግ ጠበቃና ማንም መሃይም ቢሆን አድማ በእንዲህ ዓይነት ዘዴ በአደባባይ ይደረጋል ብሎ አያስብም:: ከዚያም በላይ አድመኞቹ በኢትዮጵያ፣ በአውሮፓና በአሜሪካ የሚኖሩና ብዙዎቹም በጭራሽ የማይተዋወቁ ናቸው::

የአድማ ወንጀል ተከሳሾቹን ለመፈረጅ አስፈላጊ የሆነበት ምክኒያት አለ:: የከሳሽ ጠበቃዎች በእያንዳንዱ ተከሳሽ ላይ የወንጀለኛነት ማስረጃ ለማግኘትም ሆነ ለመከራከር ባለመቻላቸው ነው:: የሕግ አዋቂዎች እንደሚሉት ወንጀል የግል ነው:: ለከሳሽ ጠበቆች ግን፤ ፍፁም የማይተዋወቁና የማይገናኙ ሰዎችን በአንድ ከረጢት ውስጥ ከትቶ በጅምላ አድመኞች ማለት የቀለለ ነበረ::

ተከሳሾች በመጀመሪያ ላይ በጣም የታወቁ የሕግ ምሑራን ጠበቆች ነበሯቸው:: የዋስ መብትን ለማስከበር ያቀረቡት በሕገ መንግሥቱና በዓለም አቀፍ ሕጎች ላይ የተመሠረተ ክርክር ሰሚ አላገኘም:: የከሳሽ ጠበቆች ያሉት ሁሉ የሚፈፀም እየመሰለ ሄደ:: በዚህ ግዜ ሌላ ምርጫ አልነበረም ስለዚህም ከቅዱስ ዳዊት ጋር በሚከተለው ፀሎት ክርክሩን መዝጋት አስፈላጊ ሆነ

ፍታሕ ሊተ እግዚአ ወተበቀል በቀልየ
እምሕዝብ ዉፁአን እምፅድቅ

አምላክ ሆይ ከእውነት ከታቀቡና ከራቁ ሰዎች ጋር ተከራክረህ
ፍረድልኝ

ሁሉንም ነገር ለፍርድ ቤቱ ትተን ተከሳሾቹ ተመልካቾችና አድማጮች ሆንን:: ምንም እንኳን የከሳሽ ጠበቆች የሥነ ምግባር ጉድለትና በፍርድ ቤቱም ውስጥ ዙሪያችን ጠብመንጃ በያዙ ወታደሮች መከበቡ የፍርድ ቤቱን ግርማና ሞገስ ቢፈታተኑም ለፍርድ ቤቱ በበኩሌ ትልቅ ክብር አለኝ ፍርድ ቤቱ የአንድ ሀገር ሕዝብ በአንድነትና በሰላም እንዲኖር የሚያደርገው መሠረት ነው:: ከዚህም አልፎ ለዚህ ፍርድ ቤት ያለኝ ክብር በዓይነ ሕሊናዬ በግልፅ የማያቸውን በማካተት ነው

# ወንጀል እንደሊሻን

ከመስፍን ወልደማርያም

## ቃሊቲ

1ኛ፤ ከዳኞች ወንበሮች በጣም ከፍ ብሎ እግዚአብሔር የሁላችንንም ልብና አእምሮ ያያል ይፈርዳል፣ ለፈራጁም ፍርዱን ይሰጣል።

2ኛ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሕግ መጽሐፍ ከፍ አድርጎ ተሸክሞ የሕግ ያለህ ይላል።

3ኛ፤  የአፄ ሠርፀ ድንግል ሠራዊት ከደቡብ ኢትዮጵያ ገስግሶ ከቱርክ ወራሪዎች ጋር ሊፋለም ተቀላቅሎ የፈሰሰው ደምና ተቃቅፎ አፈር የሆነው አጥንት የማን ዘር ነው?  እነዚህ አፈር የሆኑት ኢትዮጵያውያን አፈር ብንሆንም በሁላችንም ውስጥ አለን ሲሉ ይሰማኛል:: በአድዋ በማይጨው በባድመም የፈሰሰው ደምና የተከሰከሰው አጥንት የማን ዘር ነው?

4ኛ፤ አክሱም ጽዮን ደብረ ዳሞና ደብረ ቢዘን በያሬድ ዝማሬ ይፀልዩልናል፣

አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ<br>
ስዳዴሆሙ ለአጋንንት<br>
ሰድዶሙ እግዚኦ እምየማንነ<br>
ወእምዛቲ መካንነ ይርሃቄ እምል፣<br>
ላእለ ይፀልእዋ ለነፍስየ

አጋንንት የምታባርሩ አብወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ከቀኛችንም ከግራችንም ከዚች ከቤታችንም (ኢትዮጵያ) ነፍሳችንን የሚጠሉትን ሁሉ አርቅልን

5ኛ፤ የእውነት መዝገቡን በግራ አጁ፤ የነፃነት ብዕሩን በቀኝ እጁ ይዞ ታሪክ ይመዘግባል፣

የከሳሽና የከሳሽ ጠበቃን ዓላማ፣ የሐሰት ድር፣ የእሥረኞቹንና የቤተሰቦቻቸውንም መጉላላት፣ የዳኞቹን ጭንቀትና ፍርድ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ኃዘንና ፀሎት፣ የዓለም አቀፉን ኡኡታና ተቃውሞ፣ በመልክ በመልኩ እያነጠረ ለሚቀጥሉት ትውልዶች ለማስተላለፍ ይመዘግባል:: እያንዳንዳችን በታሪክ ፍርድ ነፃ የምንወጣውና ወይም የሚፈረድብን የልጅ ልጆቻችንን አክብሮት የምናገኘው ወይም የምናጣው በፍሬ ሥራችን ነው::

እንግዲህ ለፍርድ ቤቱ ያለኝ ክብር እነዚህን በአጭሩ የገለፅኳቸውን ኃይሎች ሁሉ በአንድ ላይ በማጠቃለል ነው:: የከሳሹ ጠበቃ የሕጋዊም ሆነ የጨዋነት ሥነ ሥርዓት ማጣት በፍርድ ቤቱ ውስጥ ከሳሾችን ከስሰው የሚታዩት ጠብመንጃ የያዙ ወታደሮች ለፍርድ ቤቱ ያለኝን ክብር እንደሚፈታተኑት አይካድም::  ከዚም በላይ የከሳሽ ጠበቃ ያቀረበውን የክስ ድሪቶ በመቀበል የዋስትናን መብት ለተከሳሾች መንፈጉ ያሳዝናል:: በዚህ ምክኒያት እያንዳንዱ ተከሳሽ አንድ ዓመት ተኩል ያህል ከሥራ ውጭ ሆኗል::  ቤተሰቦቹ ብቻ ሳይሆኑ አገሪቱም  ተጎድታለች::  አንድ ሺህ

# <u>ወንጀል እንደሊሻን</u>

ከመስፍን ወልደማርያም

## ቃሊቲ

ያህል ሰዎች ለአንድ ዓመት ተኩል ከሥራ ውጭ ቢሆኑ አገሪቱ አንድ ሺህ አምስት መቶ የሥራ ዓመታት አጣች ማለት ነው።

ሁለተኛውን ሺህ የክርስትና ዘመን (ሚሊኒየም) እናከብራለን ብሎ በሰፊው በመደገስ ላይ ላለ ደሃ ሀገር አንድ ሺህ አምስት መቶ የሥራ ዓመታትን ማጣት የሚያሳዝን ባይሆን ኖሮ ያስቃል።

ከ1997 ምርጫ ጋር በተያያዘ የታሰርንበት የአንድ ዓመት ተኩል የግፍ እስር ከሌሎች አስረኞች ጋር ሲነፃፀር ኢምንት ነው። ወጣቶችና ሽማግሌዎች ከአምስት እስከ አሥር ዓመታት ያለ ፍርድ በቀጠሮ የሚመላለሱ ሞልተዋል። እንዲህ ያለው ግፍ በብዙ ሺህ ሰዎች ላይ የሚፈፀም ነው። ይባስ ብሎም የተፈረደባቸው ግዜአቸውን ሲጨርሱና አንዳንዶችም ፍርድ ቤት ነፃ ሲላቸው ለሳምንታትና ለወራት የሚቆዩ ሞልተዋል።

በእኛ አንድ ዓመት ተኩል ከእሥር ቤት ወደ ፍርድ ቤት መመላለስ የታዘብሁት የከሳሹ ጠበቃ ምን ያህል በሕግ የመጫወት ሥልጣን እንዳለው ነው። የቪድዮ ክምር በማስረጃነት ያቀርባል: ቅንጣት ያህል እውነት ያለባቸው ቢሆን በጣም ጥቂቶች ይሆኑ ነበር። ከዚያም በላይ እያንዳንዱ ቪድዮ ከመታየቱ በፊት የከሳሽ ጠበቃ "የምታዩትን አትመኑ እኔ የምነግራችሁን ተቀበሉ" የሚል አሰልቺ ሐሰት ይናገራል። ይህ ግዜ ከመፍጀት በቀር ምንም ዋጋ አልነበረውም። ማስረጃ ተብሎ የቀረበው የሚለውና የከሳሽ ጠበቃ የሚናገረው የሰማይና የመሬት ያህል የተራራቁና ተቃራኒዎች ናቸው። ከዚያም በላይ የቪድዮውና የምስክሮች ብዛት የሚያስገርም ነው። ሁሉም ፍሬ የሌለውና መሳቂያ በመሆኑ ያስመዘገበውን ቁጥር በጣም ለመቀነስ ተገደደ። አብዛኛው የሰነድ ማስረጃ የተባለው የሚያስቅ ነው። በበኩሌ እንኳን ማስረጃዎች የተባሉትን ክሶቹንም አላነበብኳቸውም።

የከሳሽ ጠበቃ ክሶቹን ሲያነብ ደንግጬ ደነዘዝሁ። ይህንን ጽሑፍ የምደመድመውም በዚህ የሚያቅለሸልሸኝ ክስ ነው። የትግሬ ዘር ጭራቅ እንደተነሳበት ለመገመት አያዳግትም። እስካሁን ድረስ ያልገባኝ የትግሬ ዘር ኤርትራውያንንም መጨመር አለመጨመሩ ነው። ይህ ጭራቅ ግን ከተከሰሱት መሃከል እንደማይኖር እርግጠኛ ነኝ። እንኳን በገቢር በኀልዮም ሆነ በነቢብ የትግሬን ዘር በማጥፋት ወንጀል የሚጠረጠር የለም። ቢኖር እኔ በከሳሹ ጎራ እንደምቆም አውቃለሁ።

ኤርትራውያን ባዕዶች ከዚያም ጠላቶች ተብለው ሲባረሩም ዝም ብዬ አላየሁም። በዚያን ግዜ ለዝምድናችን ብቻ ሳይሆን ለሰው ልጅ ክብርና መብት ብንቆም ኖሮ ዛሬ የትግሬን ዘር ማጥፋት ብሎ ነገር አየታሰብም ነበር። አንድ ጥፋትን በዝምታ ማሳለፍ ሌላ ጥፋትን ያስከትላል።

የወያኔ መሪዎች በሻዕቢያና በኤርትራ ሕዝብ መሀከል ትልቅ ልዩነት መኖሩን ያለመታከት ይናገራሉ። በአንጻሩ በወያኔና በትግራይ ሕዝብ መሀከል ምንም ልዩነት

http://mesfinwoldemariam.org

# <u>ወንጀል እንደሊሻን</u>

## ከመስፍን ወልደማርያም

## ቃሊቲ

አለ ብለው አያምኑም:: ወያኔ ሁሉ ትግሬ ነው  ትግሬ ሁሉ ወያኔ ነው የሚል ሰንካላ አስተሳሰብ አለ:: ፈረስ ሁሉ እንስሳ ነው ብሎ እንስሳ ሁሉ ፈረስ ነው እንደማለት ነው::

የቀረበብን ክስ የትግሬን ዘር ለማጥፋት መሆኑ ቀርቶ ወያኔን ለማጥፋት ቢሆንም የሚያቅለሸልሽ እኩይ ወንጀል ከመሆን አያልፍም:: ነገር ግን ሌላው ቢቀር ከተከሳሾቹ ውስጥ ያሉትን ትግሬዎች በማስወጣት “የትግሬ ዘር” በማለት ውስጥ ያለውን መርዛማ ዓላማ አያጋልጥም ነበር::

የትግሬ ዘር (ኤርትራውያንን ጨምሮ) የኢትዮጵያ መሠረት ነው:: የትግሬ ዘር የኢትዮጵያን ታሪክ ተሸካሚ ነው:: እንኳን በኢትዮጵያዊነታቸው ያሉትን ትግሬዎች፣ የተገነጠሉትን ለማጥፋት ማሰብ በምድርም በሰማይም ይቅርታ የማያገኝ ወንጀል ነው:: ከኤርትራ ጋር የተደረገውን የወንድማማቾች ጦርነት አጥብቄ የተቃወምኩት በዚህ ምክኒያት ነበር:: በሰሜን ያሉትን ወንድሞቻችንንና እኅቶቻችንን ከመቅጽበት ወደ ባዕድነትና ወደ ጠላትነት ለውጠን አሁን ደግሞ የተረፍነውን አጥፊና ጠፊ አድርጎ መፈረጁ ለማንም የሚበጅ አይሆንም::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ጨዋ ነው ብዬ ከልቤ ስለማምን እንዲህ ያለውን የጥፋት መርዝ ይቀበላል ብዬ አላስብም::  ራሱ ሀሳቡ መፀነሱ ያሳምማል::

የፖለቲካ አስተሳሰብ ልዩነት ወደጠላትነት ሊለወጥ አይገባም:: ምንም እንኳን ፖለቲካ ነበር ባይባልም ከአለፉት ሁለት ሥርዓቶች ጋር የፖለቲካ አስተሳሰብ ልዩነት ነበረኝ::  ሆኖም እኔ ለመቀበል አልፈለግሁም እንጂ ሁለቱም ሊሻን ሊሸልሙኝ ፈለገው ነበር::  በዛሬው ሦስተኛው ሥርዓት የፖለቲካ መብቶችን ሁሉ በሕግ መንግሥት በአዋጅ ሥርዓት ቅንጣት ያህል ማስረጃ ሳይኖረው ልዩ የወንጀል ሊሻን በግድ ለጠፈብኝ፣ ለጠፈብን፣  ይዋል ይደር እንጂ የወንጀል ልሻኑ ለሰኔ 1, 1997 እና ለጥቅምት 22, 1998 ሰማዕታት ገዳዮች <u>ያለበቀል</u> ይተላለፋል።

ክፉውን መልካም መልካሙን ክፉ ለሚሉ<br>
ጨለማውን ብርሃን ብርሃኑን ጨለማ ለሚያደርጉ<br>
ጣፋጩን መራራ መራራውን ጣፋጭ ለሚያደርጉ ወዮላቸው::

ኢሳያስ 5:20

http://mesfinwoldemariam.org